# COMMONWEALTH of VIRGINIA

## Virginia Employment Commission

First Level Appeals, P.O. Box 26441, Richmond, Virginia 23261-6441
804-786-3020 · 800-552-4500 · ፋክስ 804-786-8492


SSN:
መዝገብ:
[ቀን]

A-FLA-010

ስም
አድራሻ

ይህ ለ [ቀን] በይግባኝ መርማሪ ፊት እንዲካሄድ ቀጠሮ የተያዘለት ችሎት የስልክ ችሎት ማስታወቂያ ዛሬ በ[ቀን] ለሚከተለው ተልኳል:

COMMONWEALTH of VIRGINIA
**Virginia Employment Commission**
First Level Appeals, P.O. Box 26441, Richmond, Virginia 23261-6441
804-786-3020 · 800-552-4500 · ፋክስ 804-786-8492

# በይግባኝ መርማሪ ፊት በስልክ የሚካሄድ ችሎት ማስታወቂያ

በአቤቱታ አቅራቢ

እና

ተጠያቂ ቀጣሪ

SSN:
መዝገብ:

እና

ቀጣይ ቀጣሪ ክፍል መካከል

በዚህ ጉዳይ ላይ በቨርጂኒያ የስራ ቅጥር ኮሚሽን የይግባኝ መርማሪ ፊት ችሎት እንደሚሰማ ተገልጾልዎታል።

ችሎት መስማቱ በ **[ቀን]** በ **[ሰዓት]** ይካሄዳል።

---

- በዚህ ችሎት ላይ በስልክ ለመሳተፍ **አንዴ ይህ ማስታወቂያ ከደረስዎ በኋላ ለእኛ መደወል** እና ለችሎቱ እርስዎን እና ምስክሮችዎን ማግኘት የሚቻልባቸውን የስልክ ቁጥሮች መስጠት አለብዎ።
- **ይህን ቀደም ሲል ስልክ ቁጥር ሰጥተውን ቢሆንም እንኳ ያድርጉ።**
- ቁጥርዎን ለማስመዝገብ በስልክ ቁጥር 804-786-3020 ወይም 800-552-4500 ይደውሉ።
- በኦንላይን መመዝገብ ከመረጡ ወደ: https://va3.c2tinc.com/register/. ይግቡ።
- ቁጥርዎን ቀጠሮ ከተያዘለት ችሎት በፊት ማስመዝገብ አለብዎት። **እነዚህን መመሪያዎች የማይከተሉ ከሆነ አይደወልልዎትም።**
- በታዘዙት መሰረት ቁጥርዎን ለማስመዝገብዎ በማስረጃነት ስለሚያገለግል **የማረጋገጫ ቁጥር ማግኘትዎን** ያረጋግጡ።
  ***እባክዎ ያስታውሱ*** *– በስልክ የሚካሄዱ ችሎቶች በምስራቃዊ የጊዜ ዞን (በቀን ብርሀን ወየም መደበኛ) የሰዓት አቆጣጠር መሰረት ቀጠሮ ይያዝላቸዋል። እርስዎ የሚገኙት በምስራቃዊ የጊዜ ዞን ውስጥ ካልሆነ በጊዜ ዞንዎ ውስጥ ያለ ተመጣጣኝ ጊዜ ይሰጥዎታል።*

---

የሚከተሉት የሕግ ድንጋጌዎችና ጉዳዮች ታሳቢ ይደረጋሉ:

**ተጨማሪ የህግ ድንጋጌዎችና ጉዳዮችን ከጀርባ ይመልከቱ።**

ይህ በስልክ የሚካሄድ ችሎት ማስታወቂያ በ [ቀን] በመልዕክት ተልኳል

የኮሚሽኑ ችሎት መዝጋቢ

**በጀርባ በኩል የተገለጹትን ጠቃሚ መመሪያዎች አንብበው ይከተሉ።**

## ተጨማሪ የሕግ ድንጋጌዎች እና ጉዳዮች

## ጠቃሚ መረጃና መመሪያዎች

**በችሎት ላይ መሳተፍ:** ይህ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉበት ብቸኛው ችሎት ሊሆን ይችላል። ስለሆነም ቀጠሮ በተያዘለት ችሎት ወቅት ጉዳይዎን ለማቅረብ መዘጋጀት አለብዎት:

- **ስልክ ቁጥርዎን ማስመዝገብ እንዳለብዎት** ያስታውሱ።
- የሚሳተፉት በገመድ አልባ ስልክ ወይም በሞባይል ስልክ ከሆነ በቂ የባትሪ ቆይታ ጊዜ፣ በቂ ደቂቃዎች ያሉዎት እና በአካባቢዎ በቂ የአገልግሎት ሽፋን መኖሩን ማረጋገጥ አለብዎት። እያሽከረከሩ በሞባይል ስልክ መሳተፍ አይችሉም።
- በችሎቱ ወቅት የስልክ መስመርዎን ነጻ ያድርጉ። ይግባኝ መርማሪው እርስዎን ማግኘት ካልቻለ በችሎቱ ላይ የሚሳተፉበት እድልዎ ያመልጥዎታል።
- በችሎቱ ወቅት ፀጥ ያለ ቦታ የሚሆኑባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቹ።
- በችሎቱ ወቅት ግንኙነት የሚቋረጥብዎ ከሆነ ሳይዘጉ እንደያዙ ግንኙነትዎ እንደተቋረጠ ለማሳወቅ በስልክ ቁጥር 804-786-3020 ወይም 800-552-4500 ይደውሉ።

**ሰነድ ማስገባት:** እንዲታዩልዎት የሚፈልጓቸው ሰነዶች ካሉዎት የእነዚህን ኮፒዎች ቀጠሮ ከተያዘለት የችሎት ቀን በፊት እንዲደርሱ ለማስቻል ለመጀመሪያ ደረጃ ይግባኝ ሰሚ ቢሮ እና ለሁሉም ሌሎች ወገኖች **ወዲያውኑ** ያስገቡ። በታዘዘው መሰረት የማይቀርቡ ሰነዶች በይግባኝ መርማሪው አይታዩም። ችሎቱ በሚሰማበት ወቅት እርስዎ ያቀረቧቸው ወይም በሌሎች ወገኖች የተሰጡዎትን ሁሉንም ሰነዶች ኮፒዎች መያዝዎን ያረጋግጡ።

**ምስክሮች:** በችሎቱ ላይ የሚሳተፉ የትኛውንም አስፈላጊ ምስክሮች ማዘጋጀት አለብዎ። ከችሎቱ ቀን በፊት በዚህ ማስታወቂያ ፊት ለፊት ላይ እና በአባሪነት የተያያዘው "ጠቃሚ መመሪያዎች" ቅጽ ላይ የተገለጸውን ሥነ ሥርአት በመጠቀም የምስክሮችዎን ስልክ ቁጥሮች ማስመዝገብ ይኖርብዎታል። ምስክሮችዎን አያለማምዷቸው። ምስክርዎን የራሱን ዝርዝሮች በመጠቀም እንዲመሰክር ይፍቀዱለት።

**ማስተላለፍ**: ማስተላለፎች ሊፈቀዱ የሚችሉት ጥያቄውን መከልከል ቁሳዊና ከባድ ጉዳት እንደሚያደርስ አሳማኝ ምክንያት ሲኖር ብቻ ነው። የግድ ማስተላለፊያ መጠየቅ የሚኖርብዎ ከሆነ ይህን ወዲያውኑ በስልክ ቁጥር 804-786-3020 ወይም 800-552-4500 ለኮሚሽኑ ችሎት መዝጋቢ ማሳወቅ አለብዎት። የማስተላለፍ ጥያቄዎ የሚከለከል ከሆነ በችሎቱ ላይ ከሚቀርበው ማስረጃና ምስክርነት በመነሳት ውሳኔ ይተላለፋል። የማስተላለፊያ ጥያቄዎ ስለመፈቀዱ የማይነገርዎ ከሆነ በችሎቱ ላይ መገኘት አለብዎ።

**በይግባኝ መርማሪው ሀሳቦች አለመስማማት:** በይግባኝ መርማሪው ሀሳቦች አለመስማማቱን ይህ አለመስማማት የተመሰረተባቸውን ዝርዝሮች ካወቁ በኋላ ሆኖም ውሳኔ የተሰጠበት ቀን ሳያልፍ በአግባቡ ማካሄድ አለብዎ። አለመስማማቱ በችሎቱ ላይ ካልተደረገ በቀር በጽሁፍ መገለጽ እና ምክንያቶቹ ለዋና ይግባኝ መርማሪው መላክ አለባቸው።

**ውሳኔ**: የይግባኝ መርማሪው ውሳኔ ለተከራካሪ ወገኖች በመልዕክት ይላካሉ።: ውሳኔው ይግባኝ የማለት መብቶችዎን ያብራራል።

**መልሶ የመከፈት ጥያቄ:** የትኛውም ይግባኙ የሚመለከተው ቀጠሮ በተያዘለት ችሎት ላይ መገኘት የማይችል ወገን ጉዳዩን መልሶ የመከፈት ጥያቄ ማቅረብ ይችላል። መልሶ የመከፈት ጥያቄዎ ለምን በመልሶ መከፈቱ መፈቀድ እንዳለበት ምክንያቶቹን በመግለጽ ወዲያውኑ ለኮሚሽኑ የችሎት መዝጋቢ በጽሁፍ መሰጠት አለበት።

**መውጣት**: ይግባኙን የሚያስመዘግበው ወገን በየትኛውም ጊዜ ከይግባኙ ለመውጣት ሊጠይቅ ይችላል። የመውጫ ጥያቄው በጽሁፍ መቅረብ እና በይግባኝ ባዩ መፈረም እንዲሁም ለኮሚሽኑ ችሎት መዝጋቢ መቅረብ አለበት።

**አስተርጓሚዎች**: አስተርጓሚ የሚፈልጉ ከሆነ ይህን ወዲያውኑ ለኮሚሽኑ ችሎት መዝጋቢ ማሳወቅ አለብዎት።

**ተጨማሪ መመሪያዎች:** በተጨማሪም ውክልናን ማረጋገጥን እና መጥሪያ መጠየቅን የተመለከተ መረጃን ጨምሮ የይግባኝ ችሎትዎን እና የይግባኝ ሂደቱን የተመለከተ ጠቃሚ መረጃ ለማግኘት የይግባኝ ማስታወቂያዎን ይመልከቱ።


**የዚህን ችሎት ሥነ ሥርአት በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ካስፈለግዎት ሳይዘገዩ በ፡**
**First Level Appeals, P.O. Box 26441, Richmond, Virginia 23261-6441**
**804-786-3020 · 800-552-4500 · ፋክስ 804-786-8492**
**የሚገኘውን የኮሚሽኑን ችሎት መዝጋቢ ያነጋግሩ**